በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. 7/ሒ/1/2/816

ቀን / Date 22/9/2014

ለፍትሕ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 ማሻሻያ በተቋማችሁ በኩል እንዲመዘገብ ከዚህ በፊት መላካችን ይታወቃል፡፡

ስለዚህ የተዘጋጀውን የመመሪያ ማሻሻያ በሥራ ላይ ማዋል እንዲቻል በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 አንቀፅ 16 እንዲሁም የሚኒስትሮች ም/ቤት ግንቦት 13 ቀን 2014 ባደረገው ስብሰባ ባፀደቀው የጉምሩክ ደንብ አንቀፅ 57(1) መሠረት መመሪያው በተቋማችሁ በኩል እንዲመዘገብ የመመሪያውን ማሻሻያ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

LetterH/E

ስልክ
የፖ.ሣ.ቁ
ፋክስ/Fax

# የገንዘብ ሚኒስቴር

## አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ማሻሻያ

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

የገንዘብ ሚኒስቴር
ህዳር 2014 ዓ.ም

Disebled Dir.Was/GT

# አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ማሻሻያ

1. **አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2 **ማሻሻያ**

አካል ጉዳበኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀጽ 5 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 5 ተተክቷል፡፡

"5. ተሽከርካሪ ከቀረጥ ታክስ ነፃ ስለማስገባት የመብቱ ተጠቃሚ ሪዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ቅድመ - ሁኔታዎች በውሉ አሟልቶ ሲቀርብ፣

1. የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ሆኖ ለማሽከርከር አካላዊ ችሎታ ያለው አካል ጉዳተኛ ከሆነ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ለልዩ አውቶሞቢል ሲሆን ቢያንስ ብር 80,000 (ሰማንያ ሺህ ብር) እና የመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን ቢያንስ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆን አለበት ሲሆን፣ ከቀጣሪው አካል የደመወዙን ልክና በዚህ ደመወዙ ላይ ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እና የጡረታ አበል መቀበያ ደብተር ማቅረብ አለበት፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በግል ገቢ በሚያስገኝ ወይም የንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ባለሁለት እና ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ለልዩ አውቶሞቢል ሲሆን፣ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢ ቢያንስ 80,000 (ሰማንያ ሺህ ብር)፣ ለመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን፣ ደግሞ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር

Disebled Dir.Was/GT

3. ከመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(1)(7) ቀጥሎ የሚከተለው ተራ ፊደል (ነ) ተጨምሯል፡፡

"(ነ) ተሽከርካሪው በግዥ የተገኘ ከሆነ የተገዛበትን ደረሰኝ ወይም በስጦታ የተገኘ ከሆነ ሰጪው በሚገኝበት አገር በሚገኝ ውል አዋዋይ ሹም የተረጋገጠ የስጦታ የምስክር ወረቀት እና እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ አንድ ባለሁለት እግር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ተሽከርካሪ ወይም ልዩ አውቶሞቢል፣

በአካላዊ ችግር ምክንያት የሚሽከረከር ችሎታ የሌለው እና የማሽከርከር ችሎታ እንደሌለው በሐኪሞች ቦርድ ምርመራ እንዲሁም በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ አካል ጉዳተኛ ከሆነ ለግል አገልግሎት የሚውል አንድ መደበኛ አውቶሞቢል፣

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደአገር ማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካ መግዛት ይችላል፡፡

2/ የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(1)(ሰ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 6(1)(ሰ) ተተክቷል፡፡

"6(1)(ሰ). በተሽከርካሪው ለመገልገል የሚያስችል የፋይናንስ አቅም ያለው መሆኑን ከሚከተሉት አማራጮች በአንዱ ማረጋገጥ አለበት፡-

የመብቱ ተጠቃሚ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም በጡረታ የሚተላለፍ ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት የተከፈለው የተጣራ ደመወዝ ወይም የጡረታ አበል ለባለሁለት እና ባለሦስት እግር ወንበር የዕቃ ማስጨኛ ሰነድ፣

3/ የመመሪያው አንቀጽ 6(2)(1)(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6(2)(1)(ለ) ተተክቷል

"6(2)(1)(ለ) በአካላዊ ችግር ምክንያት የመብቱ ተጠቃሚ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ወይም ከአገር ውሰጥ መገጣጠሚያ ፋብሪካ የገዛውን ተሽከርካሪ የማሽከርከር ችሎታ የሌለው በመሆኑ በቤተሰብ አካል የሚያንቀሳቅሰው ከሆነ አስቀድሞ በሚመለከተው መስተዳድር የተረጋገጠ እና የቤተሰብ ዝርዝርን የያዘ ሕጋዊ ሰነድ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት፡፡"

4/ ከመመሪያው አንቀጽ 6(2)(1)(ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ (መ) ተጨምሯል፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

“6(2)(1)(መ) የመብቱን ተጠቃሚ ስም፣ አድራሻ ፎቶግራፍ እንዲሁም በሕክምና ተቋም የተረጋገጠውን የአካል ጉዳቱን ዓይነት እና መጠን የሚያሳይ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የመታወቂያ ወረቀት በማናቸውም ጊዜ በተሽከርካሪው ውስጥ እንዲኖር ማድረግ እና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማሳየት አለበት::

3. <u>ማሻሻያው የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከ ____________ ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል

*አዲስ አበባ _____ ቀን ____ 2014 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2